AMHARIC

CHILDREN'S SERVICES INC

# የቤተሰብዎን ቋንቋ(ዎች) ማስጠበቅ

የቤተሰብዎን ቋንቋ ማስጠበቅ ለቀጣይ የቋንቋ እድገቶች ሁሉ መሰረት ነው። ልጆችዎ በጠንካራ የቋንቋ ሞዴሎች ለማየት፣ ለመስማት እና ለመነጋገር እድሉ ሲኖራችው በቀላሉ ብዙ ቋንቋዎችን ማግኘት ይችላሉ።

በቪክቶሪያ የቅድመ አመታት ባለሞያዎች የሚመሩት በቪክቶሪያ የቅድመ አመታት የትምህርት እና ልማት ማዕቀፍ (*Victorian Early Years Learning and Development Framework* (VEYLDF)) ነው። ማዕቀፉ ብዙ ቋንቋ ተናጋሪነትን እንደ ሀብት ይገነዘባል እንዲሁም ልጆች የቤተሰብ ቋንቋቸውን እንዲጠብቁ፣ እንግሊዘኛን እንደ ተጨማሪ ቋንቋ እንዲማሩ እና የቀደምት አመታት ትምህርት እና እንክብካቤ ፕሮግራሞችን በሚከታተሉበት ጊዜ ከእንግሊዘኛ ውጭ ያሉ ቋንቋዎችን እንዲማሩ እንደሚደገፉ ግምት ያስቀምጣል (VEYLDF፣ 2016))።

የቤተሰባቸውን ቋንቋ(ዎች) በማስጠበቅ እና ማዳበርን በመቀጠል ውስጥ ለልጆችዎ ብዙ ጥቅማ ጥቅሞች አሉ።

- ልጅዎ የግንዛቤ ተለዋዋጭነታቸውን እና እድገታቸውን የእርስዎን የቤተሰብ ቋንቋ በመጠቀም ማስፋት ይችላሉ።
- የእርስዎ የቤተሰብ ቋንቋ(ዎች) መጠበቅ ለቤተሰብ ግንኙነቶች፣ ግንኙነቶችን እና የአባልነት ስሜትን ለመፍጠር አስፈላጊ ነው።
- የቤተሰብ ቋንቋ(ዎች) ከልጅዎ ማንነት፣ ባህል እና ደህንነት ጋር በማይነጣጠል መልኩ የተሳሰረ ነው።
- የቤተሰብ ቋንቋ(ዎች)ዎን አቀላጥፎ መናገር ልጆችዎ እንደ እንግሊዘኛ ያሉ ተጨማሪ ቋንቋዎችን እዲማሩ ይረዳቸዋል።

VEYLDF (2016) ለአስተማሪዎች 'የመጀመሪያ ወይም የቤት ቋንቋዎችን መማር እና ማስጠበቅ በማንነት ግንባታ ላይ ጉልህ እና ቀጣይነት ያለው ሚና እንዳለው' ያስረዳል ( ገጽg. 18)። ስለዚህ፣ የእንግሊዘኛ እንደ ተጨማሪ ቋንቋ መዳበርን የመደገፍ አስፈላጊ አካል ለአስተማሪዎች እና ለቤተሰቦች በትብብር ሽርክና ውስጥ በመሳተፍ ልጆች የቤተሰብ ቋንቋቸውን(ቋንቋዎቻቸውን) እንዲጠብቁና ማዳበራቸውን እንዲቀጥሉ ለማበረታታት እና ለመደገፍ ነው።

## በቅድመ ልጅነት ትምህርት እና እንክብካቤ አካባቢዎች ውስጥ እንግሊዘኛን እንደ ተጨማሪ ቋንቋ ማዳበር

ልጆችዎ በቪክቶሪያ የቅድመ ልጅነት ትምህርት እና እንክበካቤ አካባቢዎች ውስጥ እንግሊዝኛን የመማር ሰፊ እድል ይኖራቸዋል። ጥናቶች እንደሚነግሩን 'ልጆች እንግሊዘኛን(ወይም ሌላ ቋንቋን) ለቋንቋው በመጋለጥ፣ በግልጽ ሞዴልነት እና አዲሱን ቋንቋ ለማግኘት በበቂ ጊዜ ውስጥ እንደ ተጨማሪ ቋንቋ በተሳካ ሁኔታ መማር ይችላሉ' (VEYLDF, 2016, ገጽ. 22)።

አንድን ቋንቋ ማወቅ ልጆች ሌሎች ቋንቋዎች እንዴት እንደሚሰሩ እንዲገነዘቡ ይረዳቸዋል። ልጆች በአንድ ቋንቋ ውስጥ ያዳበሯቸው ክህሎቶች ወደ አዲሱ ቋንቋ ሊተላለፉ ይችላሉ። ልጆች አዲሱ ቋንቋ፣ ህጎቹ እና ቃላቶቹ ትርጉም የሚሰጧቸው በቤተሰብ ቋንቋ ውስጥ ነው። ልጅዎ በእንግሊዘኛ ቋንቋ አካባቢ ውስጥ ሲገባ/ስትገባ፣ እንግሊዘኛን በብዙ የተለያዩ አገባቦች የመስማት እድል ይኖራቸዋል። ለመቀላቀል እና ከሌሎች ልጆች ጋር ለመጫወት ይፈልጋሉ እና አስተማሪዎች ልጅዎ እንግሊዘኛን እንዲሰሙ እና እንዲለማመዱ ጥሩ ሞዴሎችን እና ብዙ እድሎችን ያቀርባሉ።

የቋንቋ ክህሎቶች ለልጆች የቀደመ የቋንቋ ልምዶች፣ ለአዲስ ቋንቋ ተጋላጭነት እና ለሚማሩበት አዲስ አካባቢ ምቹ በሆነ ፍጥነት እንዲያዳብሩ ይረዳቸዋል። በአንድ ጊዜ ብዙ ቋንቋዎችን የሚማሩ ልጆች ለተወሰነ ጊዜ አንዱን ቋንቋ ከሌላው የበለጠ ሊናገሩ ይችላሉ። መጀመሪያ አካባቢ ልጆች ሲናገሩ ቋንቋዎቹን ሊቀላቅሉ ይችላሉ። ቃሉን በአንደኛው ቋንቋ አውቀውት በሌላኛው ላያውቁት ይችላሉ። የንግግራቸውን ቅልጥፍና ለመጠበቅ የሚያውቋቸውን ቃላት ይጠቀማሉ። ይህ ልጆች ቋንቋዎቻቸውን በተለያዩ ቋንቋ አገባቦች ውስጥ ሲጠቀሙ የሚያዳብሩት ተፈጥሯዊ እና ተለዋዋጭ የሆነ ክህሎት ነው።

### ያስታውሱ...

በአዲስ ቋንቋ ውስጥ የንግግር ቅልጥፍናን ለማዳበር ጊዜ ይወስዳል እናም ልጆች ተጨማሪ ቋንቋ በመማር ሂደት ውስጥ በዙሪያቸው ካሉ ትልልቅ ሰዎች ጊዜ እና ግፍፊት የሌለው ድጋፍን ይፈልጋሉ።

የቤተሰባቸውን ቋንቋ(ዎች) መማር እና መጠቀም የሁሉም ልጆች መብት ነው (UNCRC, 1989)።


**ዋቢዎች**

የትምህርት እና ስልጠና ክፍል፣ 2016። *የቪክቶሪያ የቅድመ አመታት ትምህርት እና ልማት ማዕቀፍ (Victorian Early Years Learning and Development Framework)*።

UNICEF, 1989. *የተባበሩት መንግስታት የህጻናት መብት ስምምነት* (UNCRN)።